የትዳር አጋርን መምረጥ!

**27 ቱ ለትዳር የተከለከሉ ሴቶች!**

በአቡ ሀይደር

በአላህ ሥም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

ክብርና ምሥጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ይሁን (አል-ፋቲሓ 2)፡፡ የአላህ ሰላምና ውዳሴ የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነቢዩ ሙሐመድ (አል-አሕዛብ 56) ለመላው የአላህ መልክተኞች (አል-ሷፍፋት 181) የሐቅንም መንገድ በተከተለ ሁሉ ላይ ይሁን (ጣሀ 47)፡፡

1/ ፈጣሪ አምላካችን አላህ፡ ከመለኮታዊ ሥሞች አንዱ ‹‹አል-ሐኪም›› የሚለው ነው፡፡ ትርጉሙም፡- ፍፁም ጥበበኛ ማለት ነው፡፡ ጌታ አላህ ነገራትን ኹሉ በተገቢው ስፍራቸው የሚያስቀምጥ፣ ለኹሉም ነገር ተስማሚውን የሚፈጥርና የጎደለውን የሚሞላ፣ ለአማኝ ባሮቹ ዕውቀትንና ጥበብንም የሚለግስ በመኾኑ "አል-ሐኪም" ተብሎ ይጠራል፡፡ ከፍጹም ጥበበኝነቱም የተነሳ ከየ-ነገራቱ ኹላ: ጥንድ ጥንድ አድርጎ ፈጠረ፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" وَمِنْ كُلِّ شَيْءٍ خَلَقْنَا زَوْجَيْنِ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ " سورة الذاريات 49

"ትገነዘቡም ዘንድ ከነገሩ ሁሉ ሁለት (ተቃራኒ) ዓይነትን ፈጠርን፡፡" (ሱረቱ-ዛሪያት 51፡49)፡፡

2/ ሰዎችንም፡ ወንዶችና ሴቶች በማድረግ ጥንድ ጥንድ አድርጎ ፈጠረ፡፡ የፈጠራቸውንም ሰዎች በትዳር እንዲጣመሩ በማድረግ፡ አንዱ የአንዱን ክፍተት እንዲሞላ አድርጎ በማዘጋጀት ተአምራቱን አሳየ፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" وَأَنَّهُ خَلَقَ الزَّوْجَيْنِ الذَّكَرَ وَالْأُنْثَى " سورة النجم 45

"እርሱም ሁለቱን ዓይነቶች ወንድንና ሴትን ፈጠረ፡፡" (ሱረቱ-ነጅም 53፡45)፡፡

" وَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَ لَكُمْ مِنْ أَنْفُسِكُمْ أَزْوَاجًا لِتَسْكُنُوا إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُمْ مَوَدَّةً وَرَحْمَةً إِنَّ فِي ذَلِكَ لَآيَاتٍ لِقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ " سورة الروم 21

"ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አልሉ፡፡" (ሱረቱ-ሩም 30፡21)፡፡

3/ ትዳር የነቢያት ሱንና (ፈለግ) ነው፡፡ ከመጀመሪያው አባታችን ነቢዩላህ አደም (ዐለይሂ-ሰላም) ዘመን ጀምሮ የነበረ ቅዱስ ተግባር ነው፡፡ ስጋዊ ጥቅም ብቻ ሳይኾን አላህ ዘንድም ታላቅ አጅር የሚያስሰጥ ሥራ ነው፡፡

" هُوَ الَّذِي خَلَقَكُمْ مِنْ نَفْسٍ وَاحِدَةٍ وَجَعَلَ مِنْهَا زَوْجَهَا لِيَسْكُنَ إِلَيْهَا..." سورة الأعراف 189

"እርሱ ያ ከአንዲት ነፍስ (ከአደም) የፈጠራችሁ ከእርሷም መቀናጆዋን ወደርሷ ይረካ ዘንድ ያደረገ ነው..." (ሱረቱል አዕራፍ 7፡189)፡፡

" وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلًا مِنْ قَبْلِكَ وَجَعَلْنَا لَهُمْ أَزْوَاجًا وَذُرِّيَّةً وَمَا كَانَ لِرَسُولٍ أَنْ يَأْتِيَ بِآيَةٍ إِلَّا بِإِذْنِ اللَّهِ لِكُلِّ أَجَلٍ كِتَابٌ " سورة الرعد 38

"ከአንተ በፊትም መልክተኞችን በእርግጥ ልከናል፡፡ ለእነርሱም ሚስቶችንና ልጆችን አድርገናል..." (ሱረቱ-ረዕድ 13፡38)፡፡

" وَأَنْكِحُوا الْأَيَامَى مِنْكُمْ وَالصَّالِحِينَ مِنْ عِبَادِكُمْ وَإِمَائِكُمْ إِنْ يَكُونُوا فُقَرَاءَ يُغْنِهِمُ اللَّهُ مِنْ فَضْلِهِ وَاللَّهُ وَاسِعٌ عَلِيمٌ " سورة النور 32

"ከናንተም ትዳር የሌላቸውን አጋቡ፡፡ ከወንዶች ባሮቻችሁና ከሴቶች ባሮቻችሁም ለጋብቻ ብቁ የኾኑትን (አጋቡ)፡፡ ድኾች ቢኾኑ አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል፡፡ አላህም ስጦታው ሰፊ ዐዋቂ ነው፡፡" (ሱረቱ-ኑር 24፡32)፡፡

عَنْ عَبْدِ اللَّهِ قَالَ قَالَ لَنَا رَسُولُ اللَّهِ –صلى الله عليه وسلم– « يَا مَعْشَرَ الشَّبَابِ مَنِ اسْتَطَاعَ مِنْكُمُ الْبَاءَةَ فَلْيَتَزَوَّجْ فَإِنَّهُ أَغَضُّ لِلْبَصَرِ وَأَحْصَنُ لِلْفَرْجِ وَمَنْ لَمْ يَسْتَطِعْ فَعَلَيْهِ بِالصَّوْمِ فَإِنَّهُ لَهُ وِجَاءٌ ». أحمد 3466. البخاري 5065. مسلم 3464. الترمذي 1081. ابن ماجه 1845. النسائي 2239

ከዐብዱላህ ኢብኑ መስዑድ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "እናንተ የወጣት ስብስቦች ሆይ! ከናንተ መካከል የትዳርን ጣጣ መሸፈን የሚችል ካለ ያግባ፡፡ ትዳር አይንን ለመስበር እና ብልትን ከዝሙት ለመከላከል ይረዳልና፡፡ የትዳርን ጣጣ መሸፈን ያልቻለ ደግሞ፡ ፆምን በማብዛት ላይ አደራ ይበርታ፡፡ እሱ ስሜቱን ይገታለታልና" (ቡኻሪይ 5065፣ ሙስሊም 3464፣ ቲርሚዚይ 1081፣ ኢብኑ ማጀህ 1845፣ አቡ ዳዉድ 2048፣ ነሳኢይ 2239፣ አሕመድ 4104)፡፡

4/ ትዳርን መመስረት እየቻለ፡ ከትዳር የሚሸሽ ሰው ከረሱል ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሱንና እንዳፈነገጠ ይቆጠራል፡፡ በተለይም የትዳር ጣጣዎችን መሸፈን እየቻለ፡ ስሜት እያስቸገረው ከኾነ ማግባት ለሱ ዋጂብ ይኾንበታል፡፡ እራስን ከሐራም መጠበቅ ግድ ነውና፡ ስሜቱንም ከትዳር ውጭ ሊያበርድለት የሚችል አማራጭ ነገር የለምና ትዳር መመሥረት ግዳጁ ነው፡፡ በትዳር ዓለም ባል ከሚስቱ ጋር በሚያደርጉት እያንዳንዱ የፍቅር ግኑኝነትም አጅር ይኖራቸዋል፡፡

5/ ለዛሬ አላህ ፈቃዱ ከኾነ የምንመለከተው በስጋ ዝምድና ወይንም በጋብቻ ወይንም በጥብቢ ምክንያት ለትዳር ያልተፈቀዱ ወይንም የተከለከሉ ሴቶችን ነው፡፡ ለትዳር የተከለከሉ (ሐራም የኾኑ) ሴቶች ሲባል፡ ክልክልነቱ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም ‹‹ተሕሪሙን-ሙአብበድ›› እና ‹‹ተሕሪሙን ሙአቅቀት›› ይባላሉ፡፡

A. "ተሕሪሙን-ሙአብበድ" ማለት፡- ክልክልነቱ ዘላለማዊ የኾነ፡ በምንም ምክንያት ተመልሶ ሊፈቀድ የማይችል የኾነ ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ወደ አስራ ዘጠኝ 19 የሚደርሱ ለትዳር የተከለከሉ ሴቶች አሉሉ፡፡

ከ 19 ዉስጥ፡-

- 7 ቱ በስጋ ዝምድና ምክንያት (1-7)
- 7 ቱ በጥብቢ ምክንያት(8-14)
- 4 ቱ በጋብቻ መተሳሰር ሰበብ(15-18)
- 1 ዱ በመረጋገም ሰበብ(19) የተከለከሉ ናቸው፡፡

B. "ተሕሪሙን ሙአቅቀት" ማለት ደግሞ፡ ክልክልነቱ ጊዜያዊ የኾነ፡ ሐራም ያሰኘው ሰበብ በተወገደ ጊዜ ሐላል የሚኾንና ክልክልነቱ የሚነሳ ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ወደ ስምንት **8** የሚደርሱ ለትዳር የተከለከሉ ሴቶች አልሉ፡፡ ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ይቀርባል፡-

**"ተሕሪሙን-ሙአበበድ"(1-19)**

7 ቱ በስጋ ዝምድና ምክንያት (1-7)

ሀ/ ክልክልነቱ ዘላለማዊ የኾነው፡-

**1/** ወላጅ እናትን ማግባት፡**-** ይህ ማለት እኛን በቀጥታ በስጋ የወለደችን ወላጅ እናታችን፣ የአባታችንና የእናታችን ወላጅ ሴት አያታችንን፣ የወላጆቻችን አያት እያለ ወደላይ የሚወጡትንም ያካትታል፡፡

**2/** ሴት ልጆቻችንን ማግባት፡**-** የኛው የአብራካችን ክፋይ የኾኑ፡ በትክክለኛ ትዳርም ይኹን በዝሙት ከኛው የተወለዱ የጀርባዎቻችን ውጤት እስከኾኑ ድረስ፡ ከነሱ ጋር ትዳር መመስረት አይቻልም፡፡ እግረ መንገዱም፡ የልጆቻችን ልጆች፡ የነሱም ልጆች እያለ ወደታች የሚወርደው ሁሉ እዚህ ውስጥ ይካተታል፡፡

**3/** የስጋ እሕታችንን ማግባት፡**-** ከእናትና ከአባት ወይም ከሁለት አንዳቸው የምንገናኛቸው የኾኑ እሕቶቻችን ለኛ ለትዳር አይፈቀዱልንም፡፡

**4/** አክስታችንን (ዓምመት) ማግባት፡**-** የአባታችን እሕት የኾነች ሴት፡ ለኛ አክስታችን ናት፡፡ ከሷ ጋር ትዳር መመስረት አይቻልም፡፡

**5/** ሹሜዎቻችንን (ኻለት) ማግባት፡**-** የእናታችን እሕት የኾኑ (ሹሜዎቻችንን) ጋር በትዳር መጣመር አይቻልም ሐራም ነው፡፡ እነሱም በዘልማድ አክስቶቻችን ተብለው ነው የሚጠሩት፡፡

**6-** የወንድም ልጅን ማግባት፡- የስጋ ወንድማችን የወለዳቸው፣ የአብራኩ ክፋይ የኾኑ ሴት ልጆቹ፣ እኛ አጎት ልንኾናቸው የምንችል የኾኑ ኹሉ፣ ለኛ ለትዳር አይፈቀዱልንም፡፡ የነሱም የልጅ ልጆቹ እያለ ወደታች የሚወርደው ዘር ኹሉ እዚህ ውስጥ ይካተታል፡፡

**7/** የእሕት ልጅን ማግባት፡- እሕቶቻችን ትዳር መስርተው የወለዷቸው እኛ አጎት ልንኾናቸው የምንችል የኾኑ የእሕቶቻችን ልጆች፣ የነሱም የልጅ ልጆች ጋር በትዳር መጣመር አይቻልም፡፡

እነዚህ ሰባቱ በሥጋ ዝምድና ምክንያት፣ ከነሱ ጋር ትዳር ለመመስረት መቼም የማይፈቀድ የኾኑ ናቸው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" حُرِّمَتْ عَلَيْكُمْ أُمَّهَاتُكُمْ وَبَنَاتُكُمْ وَأَخَوَاتُكُمْ وَعَمَّاتُكُمْ وَخَالَاتُكُمْ وَبَنَاتُ الْأَخِ وَبَنَاتُ الْأُخْتِ..." سورة النساء 23

"እናቶቻችሁ፣ ሴት ልጆቻችሁም፣ እኅቶቻችሁም፣ አክስቶቻችሁም፣ የሹሜዎቻችሁም፣ የወንድም ሴቶች ልጆችም፣ የእኅት ሴቶች ልጆችም… (ልታገቧቸው) በእናንተ ላይ እርም ተደረጉባችሁ…" (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡23)፡፡

**<u>7 ቱ በጥብቢ ምክንያት(8-14)</u>**

**8/** የጥብቢ እናትን ማግባት፡- ይህ ማለት የሁለት ዓመት ልጅ ከመኾናችን በፊት፣ ከዘመዳችን ወይም ከጎረቤታችን የአንዷን እናት ጡት ከጠባን፣ ጥብቢውም "አንጀት አርስ" (አምስት ጊዜ ወይም ከዛ በላይ በመምጠጥ) ከነበር፣ ይህቺ ያጠባችን ሴት የጥብቢ እናታችን ነች፡፡ በመኾኑም ከሷ ጋር ትዳር መመሥረት ሐራም ይኾንብናል፡፡ የተሟላ ጥብቢ የሚባለው እስከ ሁለት ዓመት ድረስ በመኾኑ፣ የጥብቢ እናታችን የምትባለው እኛን ከሁለት ዓመት ዕድሜያችን በፊት ያጠባችን ከኾነ ብቻ ነው የሚለውን ረእይ ተከትለናል፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

**9/** የጥብቢ ልጅን ማግባት፡- ይህ ማለት ባለቤቴ አንዲትን ህጻን ብታጠባት፣ ለሷ የጥብቢ እናቷ እንደኾነችው ኹሉ፣ ለኔም ለሷ የጥብቢ አባቷ ኾኛለሁ፡፡ ልጅቷም የጥብቢ ልጃችን ኾናለች ማለት ነው፡፡ በዚህ ሰበብም የገዛ ልጄን ማግባት እንደማልችለው፣ የጥብቢ ልጄንም፣ የሷንም ልጅ፣ የልጅ ልጅ.. ማግባት አልችልም ማለት ነው፡፡

**10/** የጥቢ እሕትን ማግባት፡- ይህ ማለት፡ እኔና እሷ በስጋ ባንዛመድም፡ ነገር ግን የአንዷትን ሴት ጡት በመጥባት ከተገናኘን፡ የጥብቢ እሕቴ ኾናለች፡ የጥብቢ ወንድሟ ኾኛለሁ ማለት ነው፡፡ ያጠባችንም ሴት የጥብቢ እናታችን ኾነች ማለት ነው፡፡ በዚህ ሰበብ ከዚህች የጥብቢ እሕቴ ጋር ትዳር መመስረት አልችልም ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ፡- እኔ እና እሷ በጥብቢ መገናኘት ሰበብ መጋባት ካልቻልን፡ እኔ ከሷ እሕቶች፡ እሷ ደግሞ ከኔ ወንድሞች ጋር ኒካሕ ማሰር ትችላለች ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይኾናል፡፡ የዚህን ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለማግኘት፡ እኔና እሷን ያገናኘን ጥብቢ፡ ከማን ጡት የተወሰደ ነው? የሚለውን ማንሳት ግድ ነው፡፡ ጉዳዩ ከሶስቱ አንዱ ነው፡-

ሀ/ እኔ የሷ እናት ዘንድ ሄጄ በመጥባት፡-

ለ/ እሷ የኔ እናት ዘንድ መጥታ በመጥባት፡-

ሐ/ ሁለታችንም ከእናታችን ውጭ ሌላ ሴት ዘንድ በመጥባት፡-

ሀ/ እኔ እና እሷን የጥብቢ እሕትማማች ያደረገን፡

እኔ ከሷ እናት ዘንድ መጥቼ መጥባቴ ከኾነ፡ እሷ ለኔ የጥብቢ እሕቴ እንደኾነችው ሁሉ፡ የእናቷ ወይም የአባቷ ልጆች የኾኑ እሕቶቿ በጠቅላላ ለኔ የጥብቢ እሕቶቼ ናቸው፡፡ ከጋራ እናታቸው የጠባሁ በመኾኔ፡ ለነሱ የጥብቢ ወንድማቸው ነኝ፡፡ እንዲሁም የእናታቸው ባል ወይም የነሱ ወላጅ አባት ለኔም የጥብቢ አባቴ ነው፡፡ በመኾኑም እኔ ከሷም ኾነ ከእሕቶቿ ጋር ትዳር መመስረት አልችልም ማለት ነው፡፡ እሷ ግን ወደ ወንድሞቼ መጥታ ከነሱ ጋር ትዳር መመሥረት ትችላለች፡፡ ምክንያቱም የኔ ወንድሞች ከሷም ኾነ ከእሕቶቿ ጋር የሚያገናኛቸው ሥጋዊም ኾነ የጥብቢ ዝምድና የላቸውም፡፡ ወደ እናቷ በመሄድ የጠባሁት እኔ እንጂ ወንድሞቼ አይደሉምና፡፡ በመኾኑም እሷም ኾነች የሷ እሕቶች ከኔ ወንድሞች ትዳር መመሥረት ቢፈልጉ፡ እንዲሁም የሷ ወንድሞች ከኔ እሕቶች ትዳር መመሥረት ቢፈልጉ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ለ/ እኔ እና እሷን የጥብቢ እሕትማማች ያደረገን፡

እሷ የኔ እናት ዘንድ መጥታ በመጥባት ከኾነ ደግሞ፡ የላይኛውን ተቃራኒ ሑክም እንይዛለን ማለት ነው፡፡ እሱም፡- ከእኔ ጋር በእናት ወይም በአባት የሚገናኙ ወንድሞቼ ሁሉ ለሷ የጥቢ ወንድም በመኾናቸው ሰበብ ከነሱ ጋር ጋብቻን መፈጸም አትችልም፡፡ የጥብቢ እሕታቸው ኾናለችና፡፡ እኔ ግን ከሷ በአባትም ኾነ በእናት ከምትገናኛቸው እሕቶቿ ጋር ትዳር መመሥረት እችላለሁ፡፡ ምክንያቱም ልክ እንደሷ መጥተው ከእናቴ አልጠቡም፡ እኔም ከእናታቸው አልጠባሁም፡ የሥጋ ዝምድናም የለንምና ማለት ነው፡፡ ልክ እንደዛው ወንድሞቼ ከሷ እሕቶች፡ እሕቶቼ ደግሞ ከሷ ወንድሞች ጋር ትዳርን መመሥረት ይችላሉ ማለት ነው፡፡ በጥብቢም ኾነ በስጋ ዝምድና አልተገናኙምና፡፡

ሐ/ እኔ እና እሷን የጥብቢ እሕትማማች ያደረገን፡

ሁለታችንም ከወላጅ እናቶቻችን ውጭ የኾነች ሴት ጡት በመጥባት ከኾነ ደግሞ፡ የማንጋባው እኔ እና እሷ፡ እንዲሁም ጥብቢውን ካጠባችን ሴትዮና ልጆቿ ጋር ብቻ ይኾናል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ይህቺ ልጅ ከኔ ወንድሞች፡ እኔ  ደግሞ ከሷ እሕቶች፣ በተጨማሪም እሕቶቿ ከኔ ወንድሞች፡ ወንድሞቿ ከኔ እሕቶች ጋር ኒካሕ ለማሰር የሚከለክ

የስጋም ኾነ የጥብቢ ዝምድና አልተከሰተምና፡፡ እዚህ ላይ የተከለከለው የኔና የሷ እንዲሁም የጥቢ እናታችንና ልጆቿ ጋር በትዳር መተሳሳር ብቻ ነው፡፡ወላሁ አዕለም፡፡

**11/** የጥብቢ አክስትን ማግባት፡**-** ይህ ማለት እኔን ያጠባችኝ የጥብቢ እናቴን የባለቤቷን እሕት ማለት ነው፡፡ ሴትየዋ እኔን በማጥባቷ የጥብቢ እናቴ ነች፡፡ ባለቤቷ ደግሞ የጥብቢ አባቴ ነው፡፡ የባለቤቷ እሕቶች ለኔ የጥብቢ አክስቶቼ ናቸው፡፡ የጥብቢ አባቴ እሕት በመኾናቸው ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ከወላጅ አባቴ እሕቶች ጋር ትዳር እንደማይፈቀድልኝ ኹሉ፡ ከጥብቢ አባቴ እሕቶች (የጥብቢ አክስቶቼ) ጋርም ትዳር አልመሰርትም ማለት ነው፡፡

**12/ የጥብቢ ሹሜን ማግባት:-** ይህ ማለት፡ እኔን ያጠባቸኝ የኾነች የጥብቢ እናቴን እሕቶች ማለት ነው:: ሴትየዋ ለኔ የጥብቢ እናቴ ከኾነች፡ የሷ እሕቶቿ በጠቅላላ ለኔ የጥብቢ አክስት (ሹሜ) ይኾናሉ ማለት ነው:: የወላጅ እናትን እሕት ማግባት እንደማይቻለው ኹሉ፡ የጥብቢ እናትን እሕትም ማግባት አይቻልም ማለት ነው::

**13/ የጥብቢ ወንድሞቼን ሴት ልጆች ማግባት:-** ይህ ማለት፡ እኔ ከነሱ እናት ወይም እነሱ ከኔ እናት በመጥባት የጥብቢ ወንድማቸው ከኾንኩኝ፡ እነዚህ የጥብቢ ወንድሞቼ በትዳር የሚወልዷቸው ልጆች በጠቅላላ ለኔ የጥብቢ ወንድሞቼ ልጆች ይኾናሉ ማለት ነው:: እኔም ለነሱ የጥብቢ አጎታቸው ኾኛለሁ ማለት ነው:: የስጋ ወንድሞቼን ልጆች (እኔ አጎት የምኾናቸውን) ማግባት ክልክል እንደኾነው ሁሉ፡ የጥብቢ ወንድሞቼን ልጆችም ማግባት ክልክል ነው:: እኔ ለአባታቸው የጥብቢ ወንድም፡ ለነሱ ደግሞ የጥብቢ አጎት ነኝና::

**14/ የጥብቢ እሕቶቼን ሴት ልጆች ማግባት:-** ይህ ማለት፡ እኔ ከነሱ እናት ወይም እነሱ ከኔ እናት በመጥባት የጥብቢ ወንድማቸው ከኾንኩኝ፡ እነዚህ የጥብቢ እሕቶቼ በትዳር የሚወልዷቸው ልጆች በጠቅላላ ለኔ የጥብቢ እሕቶቼ ልጆች ይኾናሉ ማለት ነው:: እኔም ለነሱ የጥብቢ አጎታቸው ኾኛለሁ ማለት ነው:: የስጋ እሕቶቼን ልጆች ማግባት ክልክል እንደኾነው ሁሉ፡ የጥብቢ እሕቶቼን ልጆችም ማግባት ክልክል ነው:: እንደ አጎት ስለምታይ ማለት ነው::

እነዚህ ሰባቱ ደግሞ በጥብቢ ምክንያት ዝምድና የመሰረትን በመኾኑ፡ ከነሱ ጋር ትዳር መመሥረት አይቻልም ማለት ነው:: በዚህ ጉዳይ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ይላሉ:-

أَنَّ عَائِشَةَ، رضي الله عنها قالت: أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّ الرَّضَاعَةَ تُحَرِّمُ مَا يُحَرَّمُ مِنَ الْوِلَادَةِ». أحمد 26195. البخاري 2646. مسلم 3641. النسائي 3313.

"መውለድ (የስጋ ዝምድና) ሐራም የሚያደርጋቸውን በጠቅላላ ጥብቢም ሐራም ያደርጋል" (አሕመድ 26195፣ ቡኻሪይ 2646፣ ሙስሊም 3641፣ ነሳኢይ 3313)::

የስጋ ዝምድና:- ወላጅ እናትን፣ ሴት ልጅን፣ እሕትን፣ አክስትን (የአባት እሕት)፣ ሹሜን (የእናት እሕት)፣ የወንድም ልጅን፣ የእሕት ልጅን ማግባት ሐራም ካደረገ፡ ልክ እንደዛው ጥብቢም:- የጥብቢ እናትን (ያጠባችንን)፣ የጥብቢ ልጅን (ሚስቴ ያጠባቻትን የኛ ያልኾነች ሌላ

ልጅ)፣ የጥብቢ እሕትን (በአንድ ጡት የተገናኘኋት)፣ የጥብቢ አክስትን (የጥብቢ አባቴ እሕት)፣ የጥብቢ ሹሜን (የጥብቢ እናቴን እሕት)፣ የጥብቢ ወንድሜን ሴት ልጅ፣ የጥብቢ እሕቴን ሴት ልጅም ከማግባት ይከለክለኛል ማለት ነው፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡ በጥብቢ ዙሪያ ከተከለከሉት ውስጥ ሁለቱ በቁርኣን ላይ ተወስተዋል፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" حُرِّمَتْ عَلَيْكُمْ...وَأُمَّهَاتُكُمُ اللَّاتِي أَرْضَعْنَكُمْ وَأَخَوَاتُكُمْ مِنَ الرَّضَاعَةِ..." سورة النساء 23

"ከሴቶችም...እነዚያም ያጠቡዋችሁ እናቶቻችሁ፣ ከመጥባት የኾኑትም እሕቶቻችሁ በእናንተ ላይ እርም ተደረጉባችሁ..." (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡ 23)፡፡

## 4 ቱ በጋብቻ መተሳሰር ሰበብ(15-18)

**15/** የአባት ሚስትን ማግባት፡- እኛን በስጋ ያልወለደችን፣ ነገር ግን ወላጅ አባታችን ያገባት የኾነችን ሴት፡ ከአባታችን ጋር ፍቺ ብትፈጽም፡ ወይንም አባታችን ቢሞትባት፡ እኛ እሷን ፈጽሞ ማግባት አይቻለንም፡፡ እንደ እናታችን ናትና፡፡ ከአባታችን ጋር የጋብቻ ቃል ኪዳን መፈጸሟ ብቻ *(አብረው ግኑኝነት ፈጸሙም አልፈጸሙም)* በኛ ላይ ለትዳር ሐራም ትኾናለች ማለት ነው፡፡

**16/ የልጆቼን ሚስት ማግባት፡-** ከኔ የተወለዱ ወንድ ልጆቼ፡ ለትዳር ደርሰው ሴቶችን ቢያገቡ፡ በማግባታቸው ብቻ (ኒካሕ በማሰራቸው) እነሱ ያገቧቸው ሴቶች በጠቅላላ ለኔ እንደ ልጅ ይታያሉ፡፡ ስለዚህ ባሎቻቸው ቢፈቷቸው ወይንም ቢሞቱባቸው እኔ ላገባቸው አልችልም፡፡ የልጆቼ ሚስት ነበሩና፡፡ እኔም አባታቸው ነኝ፡፡

**17/ የሚስት እናትን ማግባት፡-** ከባለቤቴ ጋር የጋብቻ ቃል-ኪዳን ከፈጸምን (ኒካሕ ካደረግን) በኒካሑ ሰበብ ብቻ የሷ እናት ለኔ ሐራም ይኾኑብኛል፡፡ ለኔም የሷ እናት ልክ እንደ እኔ እናት ነው የሚታዩት፡፡ ኒካሕ ካሰርኩላት ሚስቴ ጋር አብረን ለአንድ ቀንም *ተኛን አልተኛን፡* ኒካሕ በመታሰሩ ብቻ፡ ከሷ ጋር ብፋታ እንኳ ወይም ብትሞትብኝ፡ እናቷን ማግባት ለኔ እርም ነው የሚኾነው፡፡ ከልጇ ጋር ኒካሕ ፈጽሜአለሁና፡፡

**18/ የሚስቴን ልጅ ማግባት፡-** ባለቤቴ ከኔ በፊት ሌላ ሰው አግብታ ልጅ ከወለደች፡ አሁን በባለቤቷ ሞት ወይንም መፋታት ሰበብ፡ ከኔ ጋር ትዳር ብትመሰርትና፡ ከሷ ጋር ለአንድ ቀንም አብረን ተኝተን ከኾነ፡ ከሌላ ባል የወለደቻቸው ሴት ልጆቿ በጠቅላላ ለኔ ሐራም ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ እሷ ብትሞት ወይም ብንለያይ፡ የሷን ልጆች እኔ ላገባቸው አይፈቀድልኝም፡፡ እንደ አባታቸው ነኝና፡፡ ነገር ግን ከባለቤቴ ጋር የተለያየነው፡ ወይም የሞተችብኝ፡ ከተጋባን በኋላ አንድም ጊዜ አብረን ሳናድር ከኾነ፡ ልክ እንደ እሷ፡ ልጆቿም ለኔ ለትዳር የተፈቀዱልኝ ይኾናሉ ማለት ነው፡፡ ሐራም እንዲኾኑ መስፈርቱ ከባለቤቴ (ከነሱ እናት) ጋር ከኒካሕ በኋላ አንድ ጊዜም ቢኾን የግብረ-ሥጋ ግኑኝነት መፈጸማችን ነው፡፡

እነዚህ አራቱ ደግሞ፡- በጋብቻ መተሳሰር ሰበብ ለትዳር የማይፈቀዱ አይነቶች ናቸው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" وَلَا تَنْكِحُوا مَا نَكَحَ آبَاؤُكُمْ مِنَ النِّسَاءِ إِلَّا مَا قَدْ سَلَفَ إِنَّهُ كَانَ فَاحِشَةً وَمَقْتًا وَسَاءَ سَبِيلًا •... وَأُمَّهَاتُ نِسَائِكُمْ وَرَبَائِبُكُمُ اللَّاتِي فِي حُجُورِكُمْ مِنْ نِسَائِكُمُ اللَّاتِي دَخَلْتُمْ بِهِنَّ فَإِنْ لَمْ تَكُونُوا دَخَلْتُمْ بِهِنَّ فَلَا جُنَاحَ عَلَيْكُمْ وَحَلَائِلُ أَبْنَائِكُمُ الَّذِينَ مِنْ أَصْلَابِكُمْ " سورة النساء 23-22.

"ከሴቶችም አባቶቻችሁ ያገቡዋቸውን አታግቡ፡፡ (ትቀጡበታላችሁ)፡፡ ያለፈው ሲቀር፡፡ እርሱ መጥፎና የተጠላ ሥራ ነውና...የሚስቶቻችሁም እናቶች፣ እነዚያም በጉያዎቻችሁ ያሉት የእነዚያ በእነርሱ የገባችሁባቸው ሚስቶቻችሁ ሴቶች ልጆች፣ (ልታገቧቸው) በእናንተ ላይ እርም ተደረጉባችሁ፡፡ በእነርሱም (በሚስቶቻችሁ) ያልገባችሁባቸው ብትኾኑ (በፈታችኋቸው ጊዜ ሴቶች ልጆቻቸውን ብታገቡ) በእናንተ ላይ ኀጢአት የለባችሁም፡፡ የእነዚያ ከጀርባዎቻችሁ የኾኑት ወንዶች ልጆቻችሁ ሚስቶችም (እንደዚሁ እርም ነው)..." (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡22-23)፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አሥራ ስምንቱ ክልክልነታቸው ዘላለማዊ የኾነ፡ በጊዜና በምክንያት ያልተገደበ (ተሕሪሙን ሙአብበድ) መቼም የማይፈቀዱልን የኾኑ ናቸው፡፡ እኛ ለነዚህ ለ 18 ቱም መሕረም እነሱም ለኛ (ሐሪም) መኾን እንችላለን፡፡ ከነሱ ጋር ሙሳፊር የሚያሰኝ ክልል አብሮ መጓዝ፡ አብሮ መቀማመጥ ይቻላል፡፡ እነሱ ለኛ ሐሪም፡ እኛም ለነሱ መሕረም ነንና፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

<u>1 ኛ. በመረጋገም ሰበብ (19)</u>

**19/** የተረጋገሙ ባለትዳሮች:**-** ይህ ማለት፡ ባል ሚስቱን በዝሙት ቢጠረጥራት፡ ወይንም የተወለደው ልጅ ከኔ አይደለም ብሎ ቢያስተባብል እና፡ ለዚህ ክሱም ማስረጃ ባይኖረው፣ ሚስት ደግሞ የቀረበባትን ክስ በፍጹም ብትቃወምና እሷም ማስረጃ ባይኖራት፡ የዛኔ ሁለቱም ወደ እርግማን ይጠራራሉ ማለት ነው:: እሱም ምን አይነት እንደኾነ ቀጥሎ ባለው የቁርኣን ክፍል እንዲህ ቀርቧል:-

" وَالَّذِينَ يَرْمُونَ أَزْوَاجَهُمْ وَلَمْ يَكُنْ لَهُمْ شُهَدَاءُ إِلَّا أَنْفُسُهُمْ فَشَهَادَةُ أَحَدِهِمْ أَرْبَعُ شَهَادَاتٍ بِاللَّهِ إِنَّهُ لَمِنَ الصَّادِقِينَ * وَالْخَامِسَةُ أَنَّ لَعْنَتَ اللَّهِ عَلَيْهِ إِنْ كَانَ مِنَ الْكَاذِبِينَ * وَيَدْرَأُ عَنْهَا الْعَذَابَ أَنْ تَشْهَدَ أَرْبَعَ شَهَادَاتٍ بِاللَّهِ إِنَّهُ لَمِنَ الْكَاذِبِينَ * وَالْخَامِسَةَ أَنَّ غَضَبَ اللَّهِ عَلَيْهَا إِنْ كَانَ مِنَ الصَّادِقِينَ " سورة النور 9-6

"እነዚያም ሚስቶቻቸውን (በዝሙት) የሚሰድቡ ለእነሱም ከነፍሶቻቸው በስተቀር ምስክሮች የሌሏቸው የኾኑ የአንዳቸው ምስክርነት እርሱ ከውነተኞች ለመኾኑ በአላህ ስም አራት ጊዜ ምሎ መመስከር ነው:: አምስተኛይቱም ከውሸታሞች ቢኾን በእርሱ ላይ የአላህ እርግማን ይኑርበት (ብሎ መመስከር) ነው:: እርሱም ከውሸታሞች ነው ብላ አራት ጊዜ መመስከሮችን በአላህ ስም መመስከርዋ ከእርስዋ ላይ ቅጣትን ይገፈትርላታል:: አምስተኛይቱም እርሱ ከውነተኞች ቢኾን በእርስዋ ላይ የአላህ ቁጣ ይኑርባት (ብላ መመስከርዋ) ነው::" (ሱረቱ-ኑር 24፡6-9)::

ይህ የመረጋገም ስርአት ከተከናወነ፡ ሁለቱ ተለያዩ ማለት ነው:: እስመጨረሻውም መማለስ አይችሉም:: ነገር ግን ለዘልዓለሙ ሊያገባት አይችልም ማለት፡ ከላይ እንደተጠቀሱት 18 ቱ ሴቶች፡ እሱም ለሷ መሕረም መኾን ይችላል ማለት አይደለም:: ማግባትም ኾነ ለሷ መሕረም መኾን አይችልም::ከላይ ከተጠቀሱት 18 ቱ የሚለየዉ መሕረም መሆን አለመቻሉ ነዉ::

**"ተሕሪሙን ሙአቀቀት"8 ቱ(20-27)**

**ለ/ ከልከልነቱ ጊዜያዊ የኾነው:-**

**20 / ሁለት እሕትማማቾችን በአንድ ላይ ማግባት:-** ኸዲጃና አዒሻ በአባት ወይንም በእናት የሚገናኙ እሕትማማች ከኾኑ፡ እኔ ለትዳር ከሁለት አንዱን እንጂ፡ ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ማግባት አይፈቀድልኝም፡፡ዛሬ ዓኢሻን አግብቼ ነገ ብትሞትብኝ ወይንም ብንፋታ ግን፡ ከዓኢሻ ዒድዳ (በፍቺ ወቅት የሚቆጠር ሶስት የወር አበባ መንጻት) መጠናቀቅ በኋላ እህቷን ኸዲጃን ማግባት እችላለሁኝ፡፡ የተከለከልኩት፡ ዓኢሻህ ከኔ ጋር በትዳር ሥር እያለች ወይም ዒድዳዋን ሳትጨርስ የስጋ እሕቷን ኸዲጃን ደርቦ ማግባቱ ነውና፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል:-

"..وَأَنْ تَجْمَعُوا بَيْنَ الْأُخْتَيْنِ..." سورة النساء 23

"...በሁለት እኅትማማቾችም መካከል መሰብሰብ (እንደዚሁ እርም ነው)..." (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡23)፡፡

**21/ ሴትን ልጅ ከአክስቷ ጋር ማግባት:-** ልክ እንደ እሕትማማቾች ሁሉ፡ አንድን ሴት ያገባ ሰው፡ እሷ ከሱ ጋር በትዳር ዓለም በፍቺ ወይም በሞት እስካልተለየችው ድረስ፡ የሷን አክስት (በአባትም ይኹን በእናት የምትገናኛቸውን) በሷ ላይ ደርቦ ማግባት አይቻልም፡፡ በፍች ወይም በሞት የተለየችው ጊዜ ግን አክስቷን ማግባት ይችላል፡፡ በዛው ተቃራኒ፡ የሷን የእሕት ወይም የወንድም ሴት ልጆች በሷ ላይ ደርቦ ማግባት አይቻልም፡፡ እሷ ለነሱ አክስታቸው ስለምትኾን፡ ሴት ልጅን ከአክስቷ ጋር በአንድ ማግባት አይቻልም ከሚለው ሐዲሥ ጋር መጋጨቱ አልቀረምና፡፡ ቀጣዩ ሐዲሥ ይህንን እንዲህ ያብራራል:-

عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ : ( لَا يُجْمَعُ بَيْنَ الْمَرْأَةِ وَعَمَّتِهَا ، وَلَا بَيْنَ الْمَرْأَةِ وَخَالَتِهَا ) البخاري (5109) ومسلم (1408) .

ከአቢ ሁረይራህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "ሴት ልጅን ከአክስቷ ወይም ከሹሜዋ (የእናቷ እሕት) ጋር በመሰብሰብ (ማግባት የለም)" (ቡኻሪይ 5109፣ ሙስሊም 1408)፡፡

**22/ በሶስት የተፈታች ሚስቴን ተመልሶ ማግባት፡-** ከባለቤቴ ጋር ተጣልተን፡ ሁለት ጊዜ ፈትቻት ከዛም መልሻት ሳበቃ፡ በመጨረሻም በሶስተኛው ከፈታኋት በኋላ፡ ‹‹መለስኩሽ›› ለማለት ዕድሉ የለኝም፡፡ እየፈቱ በመታረቅ መመለስ የሚቻለው ሁለት ጊዜ ብቻ ነውና፡፡ ከዛ በኋላ በመልካሙ መያዝና ተከባብሮ መኖር፡ ወይንም በቀረው ሶስተኛው ፍቺ በሰላም ማሰናበት ነው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" الطَّلَاقُ مَرَّتَانِ فَإِمْسَاكٌ بِمَعْرُوفٍ أَوْ تَسْرِيحٌ بِإِحْسَانٍ..." سورة البقرة 229

"ፍች ሁለት ጊዜ ነው፤ (ከዚህ በኋላ) በመልካም መያዝ ወይም በበጎ አኳኋን ማሰናበት ነው..." (ሱረቱል በቀራህ 2፡229)፡፡

በሶስት ከፈታኋት በኋላ ተመልሳ ከኔ ጋር በትዳር መኖር የምትችለው አንድ ነገር ሲፈጸም ብቻ ነው፡፡ እሱም፡- ሌላ ትዳር መሥርታ፡ ከዚህኛው የትዳር አጋሯ ጋር ሳትስማማ ብትለያይ እና የዒድዳ ጊዜዋን ቆጥራ እስክትጨርስ እሱም ካልመለሳት፡ ከዛ በኋላ ወደኔ ወደ ድሮ ባለቤቷ መመለስ ብትፈልግና እኔም ላገባት ብስማማ፡ እንደ አዲስ ኒካሕ ማሰር እንችላለን ማለት ነው፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" فَإِنْ طَلَّقَهَا فَلَا تَحِلُّ لَهُ مِنْ بَعْدُ حَتَّى تَنْكِحَ زَوْجًا غَيْرَهُ فَإِنْ طَلَّقَهَا فَلَا جُنَاحَ عَلَيْهِمَا أَنْ يَتَرَاجَعَا إِنْ ظَنَّا أَنْ يُقِيمَا حُدُودَ اللَّهِ وَتِلْكَ حُدُودُ اللَّهِ يُبَيِّنُهَا لِقَوْمٍ يَعْلَمُونَ " سورة البقرة 230

"(ሦስተኛ) ቢፈታትም ከዚህ በኋላ ሌላን ባል እስከምታገባ ድረስ ለርሱ አትፈቀድለትም፡፡ (ሁለተኛው ባል) ቢፈታትም የአላህን ሕግጋት መጠበቃቸውን ቢያውቁ በመማለሳቸው በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለባቸውም፡፡ ይህችም የአላህ ሕግጋት ናት ለሚያውቁ ሕዝቦች ያብራራታል፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡230)፡፡

እዚህ ጋር ልብ ልንለው የሚገባ ነገር፡- ሌላ ባል አግብታ ከሱም ተለያይታ፡ ይህም ባል ወደሱ ሳይመልሳት የዒዳ ጊዜዋ ከተጠናቀቀ፡ ወደ ድሮ ባሏ መመለስ ትችላለች ማለት፡- ከዚህኛው ሁለተኛ ባሏ ጋር ትክክለኛ ኒካሕ አስራ፡ እሱም የሷን ማር ቀምሶ፡ እሷም የሱን ማር ቀምሳ (ግኑኝነት ፈጽመው) አብረው እየኖሩ ሳለ በመሐል አለመግባባት ወይም የፍቺ ምክንያት ተከስቶ፡ ቢለያዩና እሱ ባይመልሳት ማለት ነው እንጂ፡ ቀድሞውኑ እሱ ሲያገባት ከትንሽ ቀን ቆይታ በኋላ ሊፈታትና ወደ ድሮ ባሏ እንድትመለስ ለሱ ሐላል ሊያደርጋት በማሰብ አይደለም፡፡ በዚህ መልኩ ይህን ሁለተኛ ባል ማግባት አይፈቀድላትም፡፡ **«ኒካሕ ሙሐለል»** በኛ ሸሪዓህ የተከለከለ ብሎም ድርጊቱ የሚያስረግም ህገ-ወጥ ተግባር ነውና፡፡

ዐረቦች በቅድመ ጃሂሊያ ሚስታቸውን በሶስት ከፈቱ በኋላ፡ ድጋሚ መማለስን ከፈለጉ፡ የዚህ ባል ጓደኛ ወይም ሌላ ሰው እንዲያገባትና ከዛም ፈትቶ ወደ ድሮ ባሏ እንድትመለስ ሐላል እንዲያደርግለት ገንዘብ በመክፈል ይጠይቁት ነበር፡፡ ጓደኛውም በፈቃደኝነት ይህን ተግባር ይፈጽምለት ነበር፡፡ ከዛም በሸሪዐችን ይህ ተግባር ተወገዘ፡ ብሎም እርግማንን አስከተለ፡፡ ቀጣዩ ሐዲሥ ይህንን እንዲህ ያብራራል፡-

وعَنْ عَائِشَةَ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهَا : " أَنَّ رِفَاعَةَ الْقُرَظِيَّ تَزَوَّجَ امْرَأَةً ثُمَّ طَلَّقَهَا الطلقة الثالثة فَتَزَوَّجَتْ آخَرَ فَأَتَتْ النَّبِيَّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَذَكَرَتْ لَهُ أَنَّهُ لَا يَأْتِيهَا [ أي : لا يجامعها ، وفهم الرسول صلى الله عليه وسلم أنها تريد أن تعود لرفاعة ] فقال صلى الله عليه وسلم : ( لَا ، حَتَّى تَذُوقِي عُسَيْلَتَهُ وَيَذُوقَ عُسَيْلَتَكِ [ كناية عن الدخول بها والجماع ]. رواه البخاري 5011، ومسلم 1433 .

እናታችን ዓኢሻህ (ረዲየላሁ ዐንሃ) እንዲህ አለች፡- "ሪፋዐተል-ቁረዚይ አንዲትን ሴት አገባና፡ ከዚያም ለሶስተኛ ጊዜ ፈታት፡፡ እሷም ሌላ ባል አገባች፡፡ የአላህ ነቢይ (ዐለይሂ-ሶላቱ ወስ-ሰላም) ዘንድ መጣችና እሱ (አዲሱ ባሏ) እንደማይደርስባት (እንደማይገናኛት) ነገረቻቸው፡፡ እሳቸውም፡ ወደ ድሮ ባሏ ወደ ሪፋዓህ መመለስን እንደፈለገች ተረዱ፡፡ ከዚያም፡- ‹‹ይህ (አዲሱ ባልሽ) ያንቺን ማር እስኪቀምስ፡ አንቺም የሱን ማር እስክትቀምሺ (እስትገናኙ) ድረስ (ወደ ድሮ ባልሽ መመለስ) አይኾንም›› አሏት" (ቡኻሪይ 5011፣ ሙስሊም 1433)፡፡

فعَنْ عَبْدِ اللَّهِ بْنِ مَسْعُودٍ قَالَ : " لَعَنَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ الْمُحِلَّ وَالْمُحَلَّلَ لَهُ " رواه الترمذي 1120 وصححه ، والنسائي 3416.

قال الحافظ ابن حجر رحمه الله :" وصححه ابن القطان ، وابن دقيق العيد على شرط البخاري " .

انتهى من " التلخيص الحبير " ( 3 / 372 ) .

ዐብዱላህ ኢብኑ መስዑድ (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዲህ ይላል፡- "የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ወደ ቀድሞ ባሏ እንትመለስ ሐላል የሚያደርገውን (አግብቶ ለመፍታት የሚያስበውን) እንዲሁም ሐላል የሚያስደርገውን (ወደሱ እንድትመለስለት ገንዘብ በመክፈልም ኾነ በሌላ መልኩ የሚፈልገውን) ተራግመዋል" (ቲርሚዚይ 1120፣ ነሳኢይ 3416፡ ኢብኑ ሐጀር (ረሒመሁላህ፡ ሐዲሱ ሶሒሕ መኾኑን ኢብኑ ቀጥጣን እና ኢብኑ ደቂቀል-ዒድን ዋቢ በማድረግ፡ በመጽሐፋቸው ተልኺሱል-ኸቢር 3/372 ላይ ገልጸዋል)፡፡

وقال ابن قدامة رحمه الله : " ونكاح المحلل فاسد , يثبت فيه سائر أحكام العقود الفاسدة , ولا يحصل به الإحصان , ولا الإباحة للزوج الأول , كما لا يثبت في سائر العقود الفاسدة " انتهى من "المغني" (7/ 137) .

የሐንበሊያው መዝሀብ ሊቅ ኢብኑ ቁዳማህ (ረሒመሁላህ) እንዲህ ይላሉ:- "ለቀድሞ ባለቤቷ ሐላል ለማድረግ የሚመሰረት ትዳር ብልሹ ነው። ሌሎች የተበላሹ የጋብቻ ውሎች ብይን እሱ ላይም ይጸናል። በዚህ አይነት ጋብቻ ጥብቅነት አይገኝም። (ብትፈታም) ለመጀመሪያው ባልም ሐላል የኾነች አያደርጋትም" (አል-ሙግኒ 7/137)።

وقال علماء اللجنة الدائمة للإفتاء :

" إذا تزوج الرجل المرأة بشرط التحليل ، أو نواه ، أو اتفقا عليه : فالعقد باطل ، والنكاح غير صحيح " .

انتهى من " فتاوى اللجنة الدائمة " ( 18 / 439 ) .

በስዑዲ የሚገኘው የሊቃውንት መማክርት ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ አባል እንዲህ ይላል:- ‹‹አንድ ሰው አንዲትን ሴት ወደ ቀድሞ ባሏ ለመመለስ በሚል መስፈርት ወይንም ስምምነት ወይም ያንን በማሰብ ቢያገባት፣ የጋብቻ ቃል-ኪዳኑ ውድቅ ነው፣ ኒካሑም አይሰራም›› (ፈታዋ-ለጅናህ 18/439)።

وروى البيهقي في " السنن الكبرى " ( 7 / 208 ) : عن نافع أنه قال : " جاء رجل إلى ابن عمر رضي الله عنه فسأله عن رجل طلَّق امرأته ثلاثاً ، فتزوجها أخٌ له عن غير مؤامرة منه ليحلها لأخيه : هل تحل للأول ؟ قال : لا ، إلا نكاح رغبة ، كنَّا نعد هذا سفاحاً على عهد رسول الله صلى الله عليه وسلم "

ናፊዕ እንዲህ ይላል:- "አንድ ሰው ወደ ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመር (ረዲየላሁ ዐንሁማ) ዘንድ መጣና:- የኾነ ሰው ሚስቱን በሶስት ቢፈታትና፣ የሱ ወንድም ደግሞ፣ ከፈታት ባሏ ጋር ሳይመሳጠር፣ እሷን አግብቶ ከዛም በመፍታት ወደሱ እንድትመለስና ሐላል እንድትኾን ቢያደርጋት፣ ወደ ቀድሞ ባሏ መመለስ ትችላለችን? እሱስ ሊያገባት ይበቃለታልን? በማለት ጠየቀው። ኢብኑ ዑመርም (ረዲየላሁ ዐንሁማ):- ‹‹ትዳሩ

በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እስካልኾነ ድረስ አትበቃለትም፡፡ እንዲህ አይነቱን እኛ በአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ዘመን ከዝሙት ነበር የምንቆጥረው›› በማለት መለሰለት" (አል-በይሀቂይ፡ ሱነኑል-ኩብራ 7፡208)፡፡

وقال الشيخ محمد بن صالح العثيمين رحمه الله :" إذا نوى الزوج الثاني أنه متى حلَّلها للأول طلقها : فإنها لا تحل للأول ، والنكاح باطل ، والدليل : أن هذا نوى التحليل ، فيكون داخلاً في اللعن ، وقد قال النبي عليه الصلاة والسلام : ( إنما الأعمال بالنيات ، وإنما لكل امرئ ما نوى) " انتهى من " الشرح الممتع على زاد المستقنع " ( 12 / 176 ، 177 ) .

አሽ-ሸይኽ ሙሐመድ ቢን ሷሊሕ አል-ዑሠይሚን (ረሒመሁላህ) እንዲህ ይላሉ፡- ‹‹ሁለተኛው ባሏ ለቀድሞ ባሏ ሐላል ማድረግን በማሰብ ቢፈታት፡ እሷ ለድሮ ባሏ ሐላል አትኾንም፡ ኒካሕ ማሰሩም ውድቅ ይኾናል፡፡ ማስረጃውም፡- ይህ ባል የፈታት ለቀድሞ ባሏ ሐላል ማድረግን አስቦ ነው፡፡ በዚህም ሰበብ እርግማኑ ይመለከተዋል፡፡ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ደግሞ፡- ‹‹ሥራ ሁሉ የሚለካው በሰውየው ኒያ (ልባዊ ውሳኔ) ነው፡ ሁሉም የሚየገኘው የነየተውን (በቁርጥ በወሰነው) ነው›› ብለዋልና›› (አሽ-ሸርሑል ሙምቲዕ ዓላ ዛዱል-ሙስተቅኒዕ 12/176-177)፡፡

ማሳሰቢያ፡- ይህ ሚስትን በሶስት የፈታ የሚለው፡ ‹‹ጦላቅ ረጅዒይ›› የኾነውን ለመግለጽ ነው፡፡ ማለትም፡- ሚስቱን እየፈታ እየመለሰ ሶስት ጊዜ ፍቺ ያከናወነውን ሰው በተመለከተ ነው፡፡ ነገር ግን በአንዴ ሚስቱን በሶስት የፈታ ባል፡ ልክ እንደዚህኛው ፍቺው በሶስት ተቆጥሮ፡ ሚስቱም ሌላ ባል አግብታ ያ ባልም ካልፈታትና ዒድዳዋን እስካላጠናቀቀች ድረስ አትፈቀድለትም ወይስ ፍቺው በአንዴ የተከናወነ በመኾኑ እንደ አንድ እንጂ እንደ ሶስት አይቆጠርበትም? የሚለውን አያካትትም፡፡ ይህ አይነቱ ፍቺ እንደ ሶስት ይቆጠር ወይም እንደ አንድ፡ በኢስላም ሊቃውንት መሐል ሰፊ ኺላፍ ስላለበት፡ ውሳኔ ለመስጠት በአካባቢችሁ የሚገኙ ዑለሞችን ፈትዋ በመጠየቅ፡ ከዛም በተሰጠው ፈትዋ መሠረት መሥራት ይቻላል ማለት ነው ወላሁ አዕለም፡፡

**23/ አራት ሚስቶች በስሬ ካሉ ተጨማሪ ማግባት፡-** በትዳር ዓለም አንድ ሙስሊም ወንድ በእኩልነት ማስተዳደር ከቻለ፡ እስከ አራት ሴት ድረስ ማግባት ይፈቀድለታል፡፡ በሥሩ ያሉት ሚስቶች አራት ከሞሉ፡ ከዚህ በላይ አምስተኛ መጨመር አይፈቀድለትም፡፡ አላህ ቃል እንዲህ ይላል፤-

" وَإِنْ خِفْتُمْ أَلَّا تُقْسِطُوا فِي الْيَتَامَى فَانْكِحُوا مَا طَابَ لَكُمْ مِنَ النِّسَاءِ مَثْنَى وَثُلَاثَ وَرُبَاعَ فَإِنْ خِفْتُمْ أَلَّا تَعْدِلُوا فَوَاحِدَةً أَوْ مَا مَلَكَتْ أَيْمَانُكُمْ ذَلِكَ أَدْنَى أَلَّا تَعُولُوا " سورة النساء 3

"በየቲሞችም (ማግባት) አለማስተካከላችሁን ብትፈሩ (ዝሙትንና ከተወሰነላችሁ በላይ ማግባትንም ፍሩ)፡፡ ከሴቶች ለእናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት ሦስት ሦስትም አራት አራትም አግቡ፡፡ አለማስተካከልንም ብትፈሩ አንዲትን ብቻ ወይም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን ያዙ፡፡ ይህ ወደ አለመበደል በጣም የቀረበ ነው" (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡3)፡፡

ነገር ግን ከአራቱ ሚስቶቹ አንዷ ብትሞትበት፡ ወይንም ከሚስቶቹ ካንዷ ጋር ፍቺን ቢፈጽምና የተፈታችውም ወደ ባልዋ ሳትመለስ ዒድዳዋን ብታጠናቅቅ፡ ቁጥሩ ከአራት እስካልበለጠ ድረስ በተፈታችው ወይም በሞተችበት ሚስቱ ምትክ፡ ሌላ ሴት ማግባት ይችላል፡፡ ሚስቶቹን በፍትሕ እና በእኩል የማስተዳደሩ ጉዳይ ግን እንደተጠበቀ ነው፡፡ ወላሁ አዕለም፡፡

**24/ በትዳር ያለች ጥብቅ ሴትን ማግባት፡-** ከባለቤቷ ሳትፋታና ወይንም ከባለቤቷ ተፋትታ ባለቤቷ ሳይመልሳትና የዒድዳ ጊዜዋን ሳትጨርስ፡ ወይንንም ባለቤቷ ሳይሞትባት በትዳር ያለችን ነጻ (በባርነት ቀንበር ያልወደቀች) ሴት ማግባት አይቻልም፡፡ ባለቤቷ ከፈታትና ሳይመልሳት የዒዳ ጊዜዋን ከጨረሰች፡ ወይንም ባለቤቷ ከሞተባትና የዒድዳ ጊዜዋን ከጨረሰች በኋላ ግን እሷን ማግባት ይቻላል፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" وَالْمُحْصَنَاتُ مِنَ النِّسَاءِ إِلَّا مَا مَلَكَتْ أَيْمَانُكُمْ كِتَابَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ..." سورة النساء 24

"ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ በእናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡ (ይህን) አላህ በናንተ ላይ ጻፈ...." (ሱረቱ-ኒሳእ 4፡24)፡፡

**25/ ዝሙተኛ የኾነችን ሴት ማግባት:-** በዝሙት ተግባር ላይ ያለችን ሙስሊም ሴት፡ ተውበት እስካላደረገች ድረስ፡ ጥብቁና ከዚና የራቀው ሙስሊም ወንድ እሷን ማግባት አይችልም:: በዛው ተቃራኒ በዝሙት ተግባር ላይ ያለ ሙስሊም ወንድ ከድርጊቱ ተቆጥቦ ተውበት አድርጎ ወደ አላህ እስካልተመለሰ ድረስ፡ ጥብቋ ሙስሊም ሴት እሱን ማግባት አልተፈቀደላትም:: የአላህ ቃል እንዲህ ይላል:-

" الزَّانِي لَا يَنْكِحُ إِلَّا زَانِيَةً أَوْ مُشْرِكَةً وَالزَّانِيَةُ لَا يَنْكِحُهَا إِلَّا زَانٍ أَوْ مُشْرِكٌ وَحُرِّمَ ذَلِكَ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ " سورة النور 3

"ዝሙተኛው ዝሙተኛይቱን ወይም አጋሪይቱን እንጂ አያገባም:: ዝሙተኛይቱንም ዝሙተኛ ወይም አጋሪ እንጂ አያገባትም:: ይህም በምእምናን ላይ ተከልክሏል::" (ሱረቱ-ኑር 24፡3)::

ነገር ግን፡ ዝሙተኛይቱ ሴት ከዚህ ተግባሯ ተቆጥባ ተውበት አድርጋ ከተመለሰች፡ ሙእሚኑ ወንድ እሷን ሊያገባት ይችላል:: እሱም ከዝሙት ተግባሩ ተቆጥቦ ወደ አላህም ተጸጽቶ ከተመለሰ፡ ሙእሚኗ ሴት ልታገባው ትችላለች:: አላህ ተውበትን የሚቀበል ኃጢአትን ይቅር-ባይ የኾነ ቸር አምላክ ነውና:: ቃሉም የሚለው እንዲህ ነው:-

" إِلَّا مَنْ تَابَ وَآمَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَالِحًا فَأُولَئِكَ يُبَدِّلُ اللَّهُ سَيِّئَاتِهِمْ حَسَنَاتٍ وَكَانَ اللَّهُ غَفُورًا رَحِيمًا " سورة الفرقان 70

"ተጸጽቶ የተመለሰና ያመነ መልካምንም ሥራ የሠራ ሰው ብቻ ሲቀር:: እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለውጣል:: አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው::" (ሱረቱል ፉርቃን 25፡70)::

قد سئل الشيخ محمد بن إبراهيم رحمه الله عن حكم الزواج بالزانية فقال : لا يجوز الزواج من الزانية حتى تتوب ... وإذا أراد رجل أن يتزوجها وجب عليه أن يستبرأها بحيضة قبل أن يعقد عليها النكاح وإن تبين حملها لم يجز له العقد عليها إلا بعد أن تضع حملها ... انظر الفتاوى الجامعة للمرأة المسلمة 2/ 584

አሽ-ሸይኽ ሙሐመድ ኢብኑ ኢብራሂም (ረሒመሁላህ) ዝሙተኛ የኾነችን ሴት ማግባት ሃይማኖታዊ ብይኑ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው፡ እሳቸውም ሲመልሱ:- ‹‹ዝሙተኛ የኾነች ሴት ተውበት እስኪታደርግ ድረስ ከሷ ጋር ትዳር መመስረት አይበቃም:: እሷም ተውበት ካደረገችና ሰውየውም ሊያገባት ከፈለገ ቅድሚያ ኒካሕ ሳያስር፡ እሷ ከማኅፀን እስክትጸዳ አንድ ሐይድ እስኪታይ መጠበቅ አለበት::

ሐይድ ካላየችና እርግዝና መኖሩ ከተረጋገጠ ግን የጸነሰችውን ልጅ እስክትወልድ ድረስ ከሷ ጋር ኒካሕ ማሰር አይችልም» ይላሉ፡፡ (አል-ፈታዋ አል-ጃሚዐህ ሊል-መርአቲል ሙስሊማህ 2/584)፡፡

ይህ እንግዲህ በሱረቱ-ኑር አንቀጽ 3 ላይ «ላየንኪሑ» ሚለውን ቃል ከጋብቻ ጋር በማያያዝ «አያገባም» በሚለው የተረጎሙትን ሊቃውንት ተከትለን ነው፡፡ የአማርኛው ቅዱስ ቁርኣን ተርጓሚ ሊቃውንቶችም ይህን ትርጉም መርጠዋል፡፡ ሌሎች ሊቃውንት ደግሞ፡ ቃሉን የሚፈቱት ጋብቻን ከመፈጸም ጋር ሳይኾን፡ ዚናን ከመፈጸም ጋር በማገናኘት ነው፡፡ ማለትም፡- ዝሙተኛ የኾነ ወንድ ከዝሙተኛይቱ ወይም ከአጋሪይቱ ጋር እንጂ ዚናን አይፈጽምም ማለት እንጂ አያገባም ማለት አይደለም ይላሉ፡፡ «ላ የንኪሑ» የሚለውን «አይገናኛትም» በሚለው ቃል ስለሚፈቱት ማለት ነው ወላሁ አዕለም፡፡ ለዝርዝሩ፡- (መሐመዱል-አሚን አሽ-ሺንቂጢይ፡ አድዋኡል በያን 5/417-428) ይመልከቱ፡፡

**26/ ሃይማኖት የሌላትን ሴት ማግባት፡-** ከአሕሉል ኪታብ (አይሁድና ክርስቲያን ሴት) ውጭ የኾነችን ማንኛውንም አይነት ካፊርና ሙሽሪክ ሴት፡ ከኩፍር ወጥታ እስካልሰለመች ድረስ ከሷ ጋር መቼም ቢኾን ትዳር መመስረት አይቻልም፡፡ የአላህ ቃል እንዲህ ይላል፡-

" وَلَا تَنْكِحُوا الْمُشْرِكَاتِ حَتَّى يُؤْمِنَّ وَلَأَمَةٌ مُؤْمِنَةٌ خَيْرٌ مِنْ مُشْرِكَةٍ وَلَوْ أَعْجَبَتْكُمْ وَلَا تُنْكِحُوا الْمُشْرِكِينَ حَتَّى يُؤْمِنُوا وَلَعَبْدٌ مُؤْمِنٌ خَيْرٌ مِنْ مُشْرِكٍ وَلَوْ أَعْجَبَكُمْ أُولَئِكَ يَدْعُونَ إِلَى النَّارِ وَاللَّهُ يَدْعُو إِلَى الْجَنَّةِ وَالْمَغْفِرَةِ بِإِذْنِهِ وَيُبَيِّنُ آيَاتِهِ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ " سورة البقرة 221

"(በአላህ) አጋሪ የሆኑ ሴቶች እስከሚያምኑ ድረስ አታግቡዋቸው፡፡ ከአጋሪይቱ ምንም ብትደንቃችሁም እንኳ ያመነችው ባሪያ በእርግጥ በላጭ ናት፡፡ ለአጋሪዎቹም እስከሚያምኑ ድረስ አትዳሩላቸው፡፡ ከአጋሪው (ጌታ) ምንም ቢደንቃችሁ ምእምኑ ባሪያ በላጭ ነው፡፡ እነዚያ (አጋሪዎች) ወደ እሳት ይጣራሉ፡፡ አላህም በፈቃዱ ወደ ገነትና ወደ ምሕረት ይጠራል፡፡ ሕግጋቱንም ለሰዎች ይገልጻል እነርሱ ሊገሰጹ ይከጀላልና፡፡" (ሱረቱል በቀራህ 2፡221)፡፡

የአሕሉል ኪታብን ሴት ማግባት በተመለከተ ግን፡ መሟላት ያለበት መስፈርትና ካለንበት ተጨባጭም አንጻር ምን መምሰል እንዳለበት በአካባቢያችሁ የሚገኙ ዑለሞችን በመጠየቅ መረዳት ትችላላችሁ ወላሁ አዕለም፡፡

**27/ በኢህራም ላይ ያለች ሴትን ማግባት፡-** ለሴት ልጅ የሚታሰር ኒካሕ ትክክለኛ እንዲኾን፡ የሷ ወሊይ እና ሁለት ፍትሐዊ ምሥክሮች መኖራቸው ግድ ነው፡፡ ደግሞም የልጅቷ ወሊይ ሙስሊም መኾን፣ ኒካሑን በሚያስርበት ወቅትም በሐላ

(በተፈቀደ) ሁኔታ ላይ መኾን አለበት፡፡ የሐጅ ወይንም የዑምራ ሥራን ለመፈጸም ኢሕራም አድርጎ ከኾነ፡ በኢሕራም ላይ እያለ ለራሱም ኾነ ለሰው መዳር አይችልም፡፡ ቀጣዩ ሐዲሥ ይህን ያብራራዋል፡-

لما روى مسلم (1409) عن عُثْمَانَ بْنِ عَفَّان قال قَالَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ : ( لَا يَنْكِحُ الْمُحْرِمُ وَلَا يُنْكَحُ وَلَا يَخْطُبُ ).

ዑሥማን ኢብኑ ዐፍፋን (ረዲየላሁ ዐንሁ) እንዳስተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ አሉ፡- "ሙሕሪም የኾነ ሰው (ለሐጅ ወይም ለዑምራህ ኢሕራም ያደረገ) አያገባም፡ ወሊይ ወይም ወኪል ኾኖም አያጋባምም እንዲሁም አያጭም" (ሙስሊም 1409)፡፡

በዚሕ ሐዲሥ ውስጥ ‹‹ሙሕሪም የኾነ ሰው አያገባም አያጋባምም›› የሚለው ለማግባት የሚፈልገው ባልም ይኹን፣ ለትዳር የምትፈለገው ሴቷን እና እንዲሁም ወሊይ ኾኖ ኒካሕ የሚያስረውን ሁሉ ያካትታል፡፡ (ኢብኑ ዑሠይሚን፡ አሽ-ሸርሑል ሙምቲዕ 7፡151)፡፡

እነዚህ ስምንቱ ደግሞ በምክንያት ወይንም በግዜ ላይ የተገደቡ፡ ጊዜያዊ ሐራም የኾኑ (ተሕሪሙን ሙአቅቀት) ናቸው፡፡ ሰበቡ ከተወገደ ግን ለትዳር የሚፈቀዱ የኾኑ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ካሉ ሴቶች ጋር ግን የአክስት ልጆችን፣ የአጎት ልጆችን.....መቼም ይሁን መቼ መጋባት ይቻላል፡፡ አላህ ትክክለኛውንና ሁሉንም ዐዋቂ እሱ ብቻ ነው፡፡

በዚህ መጠነኛ ዳሰሳ ላይ የተገኙ ስህተቶች ኹሉ የኔ ናቸው፡፡ ትክክል የኾነው በጠቅላላ የአላህ ተውፊቅ ነው፡፡ ማንኛውም ሙስሊም በትክክል ያለ ጥርጥር ስህተት ኾኖ ያገኘውን በጠቅላላ፡ በማረምና በማስተካከል ለወንድሞቹና ለእሕቶቹ የማሰራጨት ሙሉ መብትና ግዳጅ አለበት፡፡ የሰዎችን ስህተት በትክክል አግኝቶ በማስወገድ፡ ከአላህ የኾነውን እውነት በቦታው የሚተካን ኹሉ አላህ ይዘንለት፡፡ እኔንም ለስህተቶቼ በመላ አላህ ይቅር ይበለኝ፡፡ ወላሁ አዕለም!!

Click and Like ➤➤ https://www.facebook.com/Ustaz.Abuhyder